ECIC
Ethio Cult Info Center
DEFENDING THE DEFENCELESS

http://www.saveethiopians.net

01/01/2009

# ብርቱ የማሳሰቢያና የማስጠንቀቂያ መልእክት ለኢትዮጵያውያን

## በተለያዩ መጤ መናፍቃዊ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች ውስጥ እየሱስ ነኝ እያለ በየጸበሉ ሰይጣን ነኝ ከሚል ዜጎችን ጎጂ ውሽታም መንፈስ ተጠንቀቁ




የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ ቡድኖች መካላከያና መረጃ መዐከል (http://www.saveethiopians.net) ወደ ህዝብ ይህንን ማሳሰቢያ ወይም ማስጠንቀቂያ በዚህ አይነት መልኩ ለማውጣት የተገደደበት ምክንያት በተደጋጋሚ በቪዲዮና በተለያየ ኢንተርኔት http://www.saveethiopians.net/ ሚዲያዎች የተከታተልናቸው አይን አውጣ እየሆነ የመጣውን በጎጂ አምልኮ ቡድኖች በኩል በዜጎች ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት በህብረተሰባች መካከል በስፋት እንዲታወቅ ከማሰብ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ይህንን አይነቱ የሀይማኖትን ካባ ለብሰው በህዝብ ላይ ወንጀል የሚፈጽሙ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች ዛሬ በሰለጠነው አለም እንደፈለጋቸው እንደአገራችን ማታለልና ዜጎቻቸውን መጉዳት ያልቻሉበት ምክንያት እውነተኛ ማንነትቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች በተለያየ እንደጋዜጣ መጽሄት ኢንተርኔት ሚዲያ በመሳሰሉት በሚወጡ ማስጠንቀቂያዎች ለህዝብ በቀላሉ መቅረብ በመቻላቸው  መሆኑንን ከግምት በማስገባት ነው::

ውድ አንባቢያን የዚህ ጽሁፍ አላማ: የሀይማኖት ድርጅትን ወይም ቡድንን ለማጥላላት: ወይም የሰውን እምነት ለመንካት ሳይሆን በተለያየ ጊዜያት በቪዲዮ በካሴት በጋዜጣና በተለየየ መንገድ የተሰሙን የብዙ ዜጎች ከዘመናዊ መናፍቃን ቡድኖች አላምንም ብለው ሲወጡ በአምልኮ ስም ድርቅናው ባሳበደው በዘመናዊ መናፍቃን ቡድኖች  በኩል እየሱስ ነኝ ባይ መንፈስ (EX አዳል ሞቴ/EX ወሰን ጋላ.....ቅብጥርሴ) በህይወታቸው ላይ የደረሰ ማፍያዊ አሳዛኝ ታሪክና የመከራ ህይወት ምስክርነቶችን በማሳየት ሌሎች እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ ለማሳየት ነው::
ሌባን ራቁቱን በህዝብ ፊት አቅለው በልክስክስ ድርጊቱ ማንነቱን ካላሳወቁት ማንነቱ ሲደበቅለትና ሚስጥር ሲሆንለት ሌሎችን ለመስረቅና እየሰረቀ ያለውንም ህጋዊ መብቱ አድርጎ ለመጠቀም እንደሚሞክር ሁሉ በአምልኮ ስም የሚደረገው ወንጀል ሚስጥር በሆነ ቁጥር የሚጠቀሙት ወይም መብታቸውን የሚያስከብሩት ተጠቂ ምስኪን ደሀ ዜጎች ሳይሆኑ የሚመቸው ነፍሳቸውን: ገንዘባቸውን: መብታቸውን ሊሰርቅ የመጣ ሌባ
መንፈስና ቡድን ብቻ ነው::

ብዙ ጊዜ ከመናፍቃውያንና ከስህተት ቡድኖች መልቀቅ በመውጣት ብቻ አላምንም አልቀበልም ብሎ በህዝብ ፊት በመናገር ወይም ለራስ በማወጅ የሚያልቅ ሳይሆን የወጡ ዜጎች ቡድኑን ከለቀቁ ባሀላ የሚደርስባቸው ችግር ከቡድኑ አባላት ብቻ ሳይሆን በነበሩበት ቡድን ውስጥ ከነበረው በዜጎች ህይወት ላይ ድርቅናው ባሳበደው መመለክ አለብኝ ባይ መንፈስም ጭምር ሲሆን ይህ ደግሞ ችግሩን ለተጠቂዎቹ በጣም ከባድ የሚያደርገው ሲሆን ከውጪ ተጠቂዎቹን የሚያውቃቸውና ሊረዳቸው የሚሞክሩ ቤተሰቦችና ዜጎችም ጉዳዩን በትክክል ካለማወቅ ብዙ ጊዜ መላው ጠፍቶአቸው ግራ ሲጋቡ ይታያል:: ይህንን ግራ መጋባት ከግምት ውስጥ በማስገባት

Contact: ecic-publicrelation@saveethiopians.net   or ecic-editorial@saveethiopians.net

**ECIC**
**Ethio Cult Info Center**
DEFENDING THE DEFENCELESS

http: / /www.saveethiopians.net

**የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ ቡድኖች መካላከያና መረጃ መዐከል እንዲህ አይነት መንፈስ የሚፈልገውን ከዜጎች ህይወት ካላገኘ ዜጎች ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃቶች በጥቂቱ ከዚህ በታች ለማቅረብ ይሞክራል::**

- ይህ በጎጂ መናፍቃውያን አምልኮ ቡድኖች  በኩል እየሱስ ነኝ ብሎ የቀረባቸው መንፈስ አጋጣሚን በመጠበቅ የተለያዩ አደጋዎችን በዜጎቹ ህይወት ላይ ያደርሳል::

- ይህ በጎጂ መናፍቃውያን አምልኮ ቡድኖች በኩል እየሱስ ነኝ ብሎ የቀረባቸው መንፈስ በተለያየ በሽታና መከራ ውስጥ የግለሰቡ ህይወት እንዲገባ ያደርጋል::

- ከዚህም በላይ በሰው ሰውነት ውስጥ ይህ በጎጂ መናፍቃውያን አምልኮ ቡድኖች በኩል እየሱስ ነኝ ብሎ የቀረባቸው መንፈስ በመግባት እንደፓራሳይት በመንቀሳቀስና ግለሰቡ የተፈለገውን ካላደረገ ወይም ካልሆነ ከውስጥ የሰውነቱ ዋና ዋና ክፍሎችን እንደልብ ሳንባ ኩላሊት የመሳሰሉትን ማሳመም ዋና ዋናዎቹ በጥቂቱ ናቸው::

- በመጨረሻ ሳይጠቀስ መታለፍ የማይገበው ጉዳይ እንዲህ አይነት መጥፎ ተንኮለኛ መንፈስ በህዝብ ፊት ሲጋለጥ ካጋለጡት ዜጎች ጋር ብዙ ግዜ የሚያስቸግርና ድብብቆሽ ግብግብ የሚገጥም ሲሆን ይህ ደግሞ ይህ በመናፍቃንና ጎጂ አምልኮ ቡድኖች በኩል ሰዎችን ፍቅር ነኝ ብሎ የሚቀርብ አታላይ መንፈስን ራስ ወዳድነትና ዜጎችን አስቸገሪነት ያሳያል:: ለዚህም ምሳሌ እንዲሆን የብዙ ኢትዮጵያውያንን ገጠመኝ በድህረ ገጻችን ላይ ያወጣን ሲሆን ድህረ ገጺን ማየት ለማትሉ ወገኖች በቅርቡ በሚወጣ መጽሀፍ ላይ በሳይንሳዊና አለም አቀፋዊ መረጃ የተደገፈ ምስክርነቶች ለህዝብ እንዲቀርብ ይሆናል::

ይህንን ጉዳይ በተመለከት አለማቀፋዊነት ያላቸው ድርጅቶች (Int. Spiritual Science Research Foundation (SSRF) በቅርቡ በሪፖርታቸው ያረጋገጡት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ዛሬ ማንኛውም ኢትዮጵያው በዚህ ድህረ ገጽ አድራሻ http://www.saveethiopians.net ላይ የሚገኙትን ቪዲዮዎች ቢመለከት  ሊያረጋግጠው የሚችለው ጉዳይ ነው:: ሌላው ከተለያዩ መናፍቃዊ ጎጂ ቡድኖች በመውጣታቸው ብቻ በየጠበሉ በየስነ ልቦና ሀኪም ቤቱና በየቤቱ ወድቀው የሚገኙ ዜጎችን ህይወት በማየት ማረጋገጥ ይቻላል::

ለዚህም ነው ዛሬ **የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ ቡድኖች መካላከያና መረጃ መዐከል**  በዚህ አይነት መልኩ ይህንን በሌላው አለም የተነቃበትን በአምልኮ ስም ሙጭጭ ብሎ በሰው ነፍስ ላይ የባለቤትነትን (Possession) ጥያቄ ለማሳካት የሚደረገውን ወንጀል ማሳየት ያስገደደው:: **ይህንን አለማወቅ በህብረተሰባችን ውስጥ ለመግታትና ወንጀል እንጂ ከአምልኮ ጋር ግንኙነት የሌለው ድርጊት መሆኑን ለማሳየትና የወደፊቱ ትውልድም አምልኮን እንደማስክ እየተጠቀሙ የተለያዩ ወንጅሎችን በዜጎች ላይ የሚፈጸሙ ድርጅቶችንና አምልኩኝ ባዮቻቸውን ለይቶ አንዲያውቅ  መረጃዎችን የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ ቡድኖች መካላከያና መረጃ መዐከል በድህረ ገጹ** http://www.saveethiopians.net **ላይ ለህዝብ በስፋት የሚያቀርብ ሲሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እነዚህ አለም አቀፋዊነት ያላቸው መረጃዎች በመጠቀም ጎጂ አምልኮ ቡድኖችንና በውስጣቸው የሚሰሩ ክፉ መናፍስት ተንኮላቸውን ለይቶ እንዲያውቅ ያሳስባል::**

**በዚሁ አጋጣሚ ምን ያክል ዛሬ ኢትዮጵያውያኖች በውጪ ሀይሎች በሚመሩ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች እንደተጠቁና ብዙ ገና ስለእነዚህ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች ያላወቁ ቡድኖች በእነዚህ ቡድኖች ማታለል ሊጠመዱና ነገ ተጠቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማየት ይችሉ ዘንድ እነዚህ ቪዲዮዎች ከኢንተርኔት ላይ እንዲመለከቱ አደራ እንላለን::**

Contact: ecic-publicrelation@saveethiopians.net   or ecic-editorial@saveethiopians.net

